የሰ/መ/ቁ. 52041

ሰኔ 29 ቀን 2002 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

አመልካች፡- የእርሻ መሣሪያዎችና የቴክ/አ/ማኅበር - ነ/ፈጅ ጌታቸው ደገ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- የኢት/መድን ድርጅት - ነ/ፈጅ ጽጌረዳ ተሻገር - ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት እንዲመረመር የቀረበው የአ/አ/ ከተማ ማኅበራዊ ፍ/ቤት የግራ ቀኙ ክርክር የመዳኘት ሥልጣን በተመለከተ ነው፡፡ የጉዳዩ አጀማመር ሲታይ ተጠሪ ከሣሽ አመልካች ተከሣሽ ነበር፡፡ የተጠሪ የክስ ምክንያት ንብረትነቱ የአመልካች የሆነው መኪና የተጠሪን ደንበኛ መኪና ገጭቶ ጉዳት አድርሷል በሚል ተጠሪ የከፈለውን ብር አራት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰባ ሰባት /4977.00/ አመልካች እንዲተካ እንዲወሰን የሚል ነው፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣን የተመለከተው በአ/አ ከተማ በቂርቆስ ክ/ከተማ የቀበሌ 04 ማኅበራዊ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ እንደ ክሱ አቀራረብ ወስኗል፡፡ በይግባኝ ሰሚ የአ/አ ከተማ ፍርድ ቤቶችም ይኸው ውሣኔ ፀንቷል፡፡

ለዚህ ሰበር ከቀረበው አቤቱታ አንፃር ይህ ችሎት የተመለከተው ማኅበራዊ ፍ/ቤቱ ይህንን ጉዳይ የመዳኘት ሥልጣን አለው ወይስ የለውም? የሚለውን ሲሆን በዚህ ረገድ የተጠሪ ነ/ፈጅ ባቀረቡት የክርክር መልስ በአዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 50 መሠረት ማኅበራዊ ፍርድ ቤት እስከ ብር አምስት ሺህ በሆነ የፍትሐብሔር ጉዳይ አከራክሮ የመወሰን ሥልጣን አለው ሲሉ የሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ እንዲፀና ጠይቀዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል ባጭሩ የተመለከትነው ሲሆን እኛም ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ሕጉን አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከመዝገቡ መረዳት የተቻለው የተጠሪ ክስ ምክንያት ከውል ውጪ ኃላፊነት የሚመለከት ሲሆን ለመክስ መነሻው ግን ተጠሪ ከደንበኛው ጋር አለኝ በሚል የመድን ውል መነሻ በንግድ ሕጉ በተመለከተው የመዳረግ መብት የቀረበ ስለመሆኑ ነው። በዚህ መዝገብ የቀረቡት ተከራካሪ ወገኖች አንደኛው ብቻ ሳይሆን ሁለቱም በፌዴራል መንግሥት የተመዘገቡ ወይም የተቋቋሙ ስለመሆናቸውም መረዳት ችለናል። ስለሆነም በዚህ መነሻ የቀረበውን የዳኝነት ጥያቄ ተቀብሎ ለመወሰን የአ/አ ከተማ ማኅበራዊ ፍ/ቤት ሥልጣን አለውን? ለሚለው ጥያቄ ምላሽ ለማግኘት በተጠሪ የተጠቀሰውን አዋጅ ቁጥር 361/95 ከአዋጅ ቁጥር 25/88 ጋር በማገናዘብ መመርመር ያስፈልጋል። የአ/አ ከተማ ፍርድ ቤቶችና የመዳኘት ሥልጣን የተሰጣቸው አካላት አደረጃጀት እና ሥልጣንና ኃላፊነት በተመለከተ በአዋጅ ቁጥር 361/95 ከአንቀጽ 39-50 ድረስ ተደንግጎ እናገኛለን። ከእነዚህ ድንጋጌዎች አጠቃላይ ይዘት መገንዘብ የሚቻለው የዳኝነት አካላቱ ሥልጣን መሠረት ያደረገው የከተማው አስተዳደር ተቋማት ተግባር እና ኃላፊነት በሚመለከቱ አስተዳደራዊ ጉዳዮች እንዲሁም በከተማው ነዋሪዎች መካከል የሚነሱ የፍትሐብሔር እና የደንብ መተላለፍ ጉዳዮች ላይ አከራክሮ የመወሰን ኃላፊነት የተሰጠ ስለመሆኑ ነው። በተለይም ከተያዘው ጉዳይ ጋር አግባብነት ያለው የአዋጁ አንቀጽ 50/1/ የክርክር መጠኑ ከብር አምስት ሺህ ያልበለጡ የንብረት እና የገንዘብ ክርክሮችን ማኅበራዊ ፍ/ቤቶች እንዲዳኙ ሥልጣን ሲሰጥ ከፍ ሲል ከተመለከተው አጠቃላይ ዓላማ እና ወሰን ጋር መታየት ያለበት መሆኑን መገንዘብ አዳጋች አይደለም።

በዚህም እጅግ ቀላል የሆኑ ጉዳዮች እና ውስብስብ የሕግ ጥያቄ የማያስነሱ ክርክሮች በአጭር እና በቅርበት ለማኅበረሰቡ አገልግሎት እንዲሰጡ ማስቻል ስለመሆኑ መረዳት የሚቻል ነው። የአዋጁ ግብ ይህ መሆኑ የሚታወቅ ሆኖ የገንዘብ መጠኑ ከብር አምስት ሺህ በታች በመሆኑ ብቻ በማናቸውም ጉዳዮች ላይ የመወሰን ሥልጣን ያሰጠዋል የሚለውን የተጠሪ ክርክር ከአዋጅ ቁጥር 25/88 አንፃር መመልከት ተገቢ ይሆናል። የአዋጅ ቁጥር 25/88 የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን የዳኝነት ሥልጣን ሲዘረዝር በዋነኛነት ታሳቢ ያደረገው የፌዴራል መንግሥት አወቃቀር እና የፌዴራል ሥርዓቱን የሥልጣን ክፍፍል መርህ በመጠበቅ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። ስለሆነም የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የሥልጣን ወሰን በግልጽ በሌላ ሕግ እስካልተሻረ ድረስ በዝምታ ወይም ኋላ በወጣ ሕግ ተተክቷል ሊባል አይችልም። ስለሆነም በተጠሪ በኩል የቀረበው ክርክር ማለትም በአዋጅ ቁጥር 25/88 የተደነገገው ቢኖርም አዋጅ ቁጥር 361/95 ኋላ የወጣ በመሆኑ ተፈፃሚነት አለው የሚለው ክርክር ተቀባይነት ያለው አይደለም። ይልቁንም በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 5/6/ እና 5/9/ ሥር በግልጽ እንደተደነገገው በፌዴራል መንግሥት የተቋቋመ ተቋም ተከራካሪ የሆነበት ጉዳይ ከመሆኑ አንፃር እና የክርክሩ መነሻም የመድን ውል መሆኑ ሲታይ በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የዳኝነት ሥልጣን የፌዴራል ፍርድ ቤቶች መሆኑ በግልጽ በሕግ የተደነገገ ጉዳይ መሆኑን ነው።

ስለሆነም ለፌዴራል ፍርድ ቤቶች በግልጽ በተሰጠ የዳኝነት ሥልጣን የገንዘብ መጠኑን ብቻ መሠረት በማድረግ የአ/አ ከተማ ማኅበራዊ ፍ/ቤት ሥልጣን ነው በማለት በተጠሪ በኩል የቀረበው ክርክር ተቀባይነት ያለው አይደለም ብለናል።

ስለዚህ በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር ላይ ያሉት ተከራካሪ ወገኖች ማንነት እና በክርክሩ የሚነሳው የሕግ ጥያቄን መሠረት በማድረግ ከአዋጅ ቁጥር 25/88 አንፃር ተመልክቶ ባለው አግባብ ሊስተናገድ የሚገባው ሆኖ ሳለ የአ/አ ከተማ ማኅበራዊ ፍ/ቤት ተቀብሎ የሰጠው ፍርድ የሥረ-ነገር ሥልጣን በሕግ በግልጽ ያልተሰጠው በመሆኑ ሊፀና የሚችል ፍርድ የለም ብለናል።

ስለሆነም የማኅበራዊ ፍርድ ቤቱ ይህንኑ ተገንዝቦ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 231/1/ለ/ መሠረት መዝገቡን መዝጋት ሲገባው በጉዳዩ ላይ ውሣኔ መስጠቱ የመሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተናል። ስለዚህም ተከታዩን ውሣኔ ሰጥተናል።

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

በቂርቆስ ክ/ከተማ የቀበሌ 04 ማኅበራዊ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 953/97 የሰጠው ውሣኔ፣ የአ/አ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 02451 የሰጠው ፍርድ እና የአ/አ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 08207 በ20/02/2002 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል።